ፖቨርቲ አክሽን ኔትወርክ ኦፍ ሲቪል ሶሳይቲ ኦርጋናይዜሽንስ ኢን ኢትዮጵያ(ፖአኔኢ)

# የአየር ንብረት ለውጥ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችና በፈጣንና የዘላቂ ልማት ድህነትን የማስወገድ መርሀ-ግብር አፈጻጸም ሳይ የሚኖረው ተፅዕኖ

## የፖሊሲ ማሻሻያ ሃሳቦች

ታህሳስ 2002 ዓ.ም
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

በዳንቸርች ኤይድ የገንዘብ ድጋፍ የተካሄደ ጥናት

© ይህ አጭር ሰነድ በፖቨርቲ አክሽን ኔትወርክ ኦፍ ሲቪል ሶሳይቲ ኦርጋናይዜሽንስ ኢን ኢትዮጵያ (ፖአኔኢ) የተዘጋጀ ሲሆን ከዋናው የጥናት ሰነድ የተጨመቁ ፍሬ ሃሳቦችን የያዘ ነው።

## አድራሻ

ከቅዱስ ገብርኤል ሆስፒታል ፊት ለፊት ከአውራሪስ ሆቴል ገባ ብሎ

ቦሌ ክፍለ ከተማ፤ ቀበሌ 06 የቤት ቁጥር 468

የመልእክት ሳጥን ቁጥር 2433 Code 1250 አዲስ አበባ

ስልክ: +251 11 663 96 79/663 94 28

ፋክስ: +251 11 663 59 65

ኢ.ሜይል: pane@ethionet.et

ዌብ ሳይት: www.pane.org.et

## አጥኚዎች

ዶ/ር ሳትሽኩማር ቤሌታታን

አቶ ይትባረክ ጥበበ

አቶ ግሩም ወ/ጊዮርጊስ

## መግቢያ

የአየር ንብረት ለውጥ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካትና ድህነትን ለማስወገድ ኢትዮጵያ በቀረጻቻቸው መርሀ-ግብሮች አፈጻጸም ላይ እያደረሰ ያለው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ እንደሆነ ይገመታል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ ለመቀነስና ለመከላከል የሚያስችል የመቋቋም አቅም መፍጠርና ማጠናከር ደግሞ እንደአማራጭ የሚወሰድ ሳይሆን እንደ ዋነኛ ስልት ሆኖ መወሰድ ያለበት ጉዳይ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖን የመቋቋም አቅም መፍጠርና ማጠናከር ስልት መኖር ኢትዮጵያ የቀረጸችውን የድህነት ማስወገጃና የዘላቂ ልማት መርሀ-ግብር በተፋጠነ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ያስችላታል፡፡

ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ በአሁኑ ወቅት የአየር ንብረት ለውጥ በኢትዮጵያ ውስጥ እያሳደረ ያለውን ተፅዕኖ የሚያመለክቱ በጥናት ላይ የተደገፉ መረጃዎች በተፈለገው መልኩ የሉም፡፡ ፖቨርቲ አክሽን ኔትወርክ ኦፍ ሲቪል ሶሳይቲ ኦርጋናይዜሽንስ ኢን አትዮጵያም (ፖአኔኢ) ይህንን የመረጃ ክፍተት በመገንዘብ "የአየር ንብረት ለውጥ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦችና በፈጣንና የዘላቂ ልማት ድህነትን የማስወገድ መርሀ-ግብር አፈጻጸም ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ" በሚል ጥናት አካሂዷል፡፡

ጥናቱ በየደረጃው ባሉ አካላት ዘንድ የአየር ንብረት ለውጥ በኢትዮጵያ ውስጥ እያደረሰ ያለውን ተፅዕኖ እንዲገነዘቡና ለችግሩ መፍትሔ እንዲፈልጉ ከማስቻሉም በላይ መንግስት በቀጣይ በሚቀረጸው የዘላቂ ልማትና የድህነት ማስወገጃ መሀ-ግብር ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይን ለማካተት እንዲቻል ጥናቱ እንደ ዋነኛ ግብዓት ሆኖ እንደሚያገለግል ፖአኔኢ እምነቱ ነው፡፡

## ከዋናው የጥናት ሰነድ የተውጣጡ ፍሬ ሃሳቦች በአጭሩ

ከጊዜ ወደ ጊዜ እያየለ የመጣው የዓለም ሙቀት መጨመርና በዚህም የተነሳ እየጨመረ ያለዉ የአየር ንብረት ለውጥ ክስተት በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና፣ የሃይል አቅርቦት፣ የድህነት ቅነሳና የዘላቂ ልማት ጥረቶች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ በማሳደር፣ እንዲሁም የተፈጥሮ ሃብቶች ጉስቁልና እና የተፈጥሮ አደጋዎችን ከፍ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ፈተና የጋረጡ ተግዳሮቶች ናቸዉ። በዚህም ምክንያት በኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች እና የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራምን ለማሳካት አስቸጋሪ እንዲሆን ያደርጋል።

ይህ አጭር ጥናታዊ ጽሁፍ በዴስክ ጥናት ላይ በመመስረት ከተካሄደው ጥናት ባጭሩ የተውጣጡ ፍሬ ሃሳቦችንና የፖሊሲ ማሻሻያ ሃሳቦችን አካቶ የተዘጋጀ ሰነድ ነው። የዴስክ ጥናቱ የተለያዩ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ሰነዶች በማጣቀስና በማገናዘብ ለውጡ በኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግብ እና የዘላቂ ልማትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ላይ የሚኖረውን ተፅዕኖ ለማሳየት ሞክሯል። በተጨማሪም የአለም ባንክን የዳሰሳ ጥናት ዘዴ በመጠቀም የአየር ንብረት ለውጥ በሀገሪቱ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነዶች ላይ መካተትና አለመካተታቸውን ገምግሞአል። በተጨማሪም የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ በሀገሪቱ ውስጥ ያሉ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ያላቸውን ግንዛቤና እይታ እና ሃሳብ ለማካተት ተሞክሯል።

በጥናቱ ውጤት መሰረት ለኢትዮጵያ በአየር ንብረት መለዋወጥ እና ለውጥ ተጋላጭነት መንስኤ ከሆኑት ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ የአገሪቱ የግብርና ዘርፍ በዝናብ ላይ ጥገኛ መሆኑ ነው። የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በአብዛኛው በግብርና ላይ የተመሰረተ መሆኑ ሀገሪቱን ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ ያደርጋታል። የአየር ንብረት ለውጥ በኢትዮጵያ በእርሻ እና በከብት እርባታ ዘርፎች ላይ ከሚያሳየዉ ተፅእኖ በተጨማሪ በሃገሪቱ የውሃ ሀብት፣ በሃይል ማመንጨት አቅሚ ላይ፣ ብሎም በአጠቃላይ ኢኮኖሚዋ ላይ በሚያሳድረው ተፅዕኖ የተነሳ በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦቿና በድህነት ቅነሳ ጥረቷ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር ኢትዮጵያ ያለመችዉን የኢንዱስትሪ ልማት መፋጠንና ያቀደቻቸውን እንደ ቱሪዝም ያሉ የአገልግሎት ዘርፎች መሻሻል እውን ለማድረግ አስቸጋሪ ይሆናል።

በሌላ በኩል አብዛኛዉ የከተማ ነዋሪ የአካባቢ ንጽህና አገልግሎት ባልተሟሉባቸው አካባቢዎች ተፋፍኖ መኖርም የአየር ንብረት ለውጥ የከተማ ነዋሪውን ወደማይወጣው ዘርፈ ብዙ የድህነት

ወጥመድ የማስገባት ተጨማሪ ሚና እንዳለዉ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል በገጠር ነዋሪውም ላይ በሚያደርሰው ተፅዕኖ ምክንያት ስደት እና መፈናቀልን ሊያባብስ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ግጭቶች ሊከሰቱ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በኢትዮጵያ በርካታ አካባቢዎች በሚኖረው የአርብቶ አደሩ ህብረተሰብ የአኗኗር ሁኔታ ላይም የአየር ንብረት ለውጥ የሚኖረው ተፅእኖ ከፍተኛ ነዉ፡፡ ከአገሪቱ ህዝብ ውስጥ አብዛኛውን ድርሻ የሚወስዱት ሴቶች እና ህፃናትም በአየር ንብረት ለውጡ ምክንያት በከፍተኛ ሁኔታ ለጥቃት ከሚጋለጡ የህብረተሰብ ክፍሎች ቀዳሚዎቹ ይሆናሉ፡፡ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ ለሚከሰቱ የጤና ችግሮች ኢትዮጵያ በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጭ ናት፡፡ በአሁኑ ወቅት የአገሪቱ 68% የቆዳ ስፋት ያለው አካባቢ ለወባ በሽታ ተጋላጭ ሲሆን የአየር ንብረት ለውጥ ደግሞ የወባ በሽታ ስርጭት በከፍተኛ ሁኔታ እንዲባባስ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በዚህም የተነሳ በወባ ወረርሽኝ ሊጠቃ የሚችለዉ ህዝብ ቁጥርም በከፍተኛ መጠን ሊጨምር እንደሚችል ይገመታል፡፡ በተጨማሪም የአየር ንብረት ለውጥ በአገሪቱ የብዝሃ ህይወት ሀብት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ በማድረስ በርካታ የእጽዋትና የእንስሳት ዝርያዎች ቁጥር እንዲመናመን ብሎም እንዲጠፉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ይሁንና የአየር ንብረት ለውጥ በኢትዮጵያ እያደረሰ ስላለው ተጽዕኖ በተቀናጀና በተደራጀ መልክ ተመዝግቦ አይገኝም፡፡ ስለዚህ ይህ አጭር ጥናታዊ ዳሰሳ የአየር ንብረት ለውጥ በቁሳዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በማህበራዊ ገጽታ ላይ የሚያደርሰውን ተፅዕኖ ለመረዳትና በወቅታዊ መረጃ ላይ የተመሰረቱ ፖሊሲዎችን የማውጣትና የድህነት ቅነሳ ፕሮግራሙን የመቃኘት አስፈላጊነትን ያመላክታል፡፡ ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ አካባቢያዊ ጥናትና ምርምር ማድረግ እና የአየር ንብረት ለውጡን ተጽእኖ በልዩ ልዩ የአገሪቱ የአየር ንብረት ቀጠናዎች (agro-ecological zones) ለይቶ ማወቅን ይጠይቃል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የአየር ንብረት ለውጥ በአለም አቀፍ ደረጃ አስከፊ ድህነትን ለመቀነስ የተቀመጡትን የምዕተ አመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት በሚደረጉት ጥረቶች ላይ ከፍተኛ ፈተና መጋረጡ ግልፅ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የአየር ንብረት ለውጥ መዘዝ የአስከፊ ድህነት ገፅታ የሆኑትን ዝቅተኛ ገቢ፣ ርሃብ፣ እርዛት፣ በሽታ፣ የበቂ መጠለያ እጥረት፣ ወዘተ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የጾታ፣ የትምህርት እንዲሁም የአካባቢ ደህንነትን ለማረጋገጥ እ.ኤ.አ. የ2000ውን የተባበሩት መንግስታት ጉባኤን አቋም ተፈጻሚ ለማድረግ እ.ኤ.አ. በ2001 የተቀረጹትን የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት ከፍተኛ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡ በዚህም የተነሳ የአየር ንብረት

ለውጥ በአሁኑ ወቅት እንደ አንድ የአካባቢ ሁኔታ ጉዳይ ከመታየት አልፎ የልማት፣ የድህነት ቅነሳ፣ የምግብ ዋስትና፣ የኢኮኖሚ፣ የጤና፣ የሰብአዊ መብት፣ የአስተዳደር እና የእኩልነት ጉዳይ ሆኗል፡፡ በአጭሩ የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ጉዳይ ሆኗል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ መሠረታዊ የሰብአዊ መብት ጉዳዮች ሆነው በአለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎችና በምዕተ ዓመቱ የተባበሩት መንግስታት የአቋም መግለጫ የተካተቱትን የጤና አገልግሎት፣ የትምህርት፣ መጠለያ የማግኘት እና ደህንነት መብቶች ከማስከበር አንፃርም አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በኢትዮጵያ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ማሳካት ማለት የብዙዎችን በህይወት የመኖር ተስፋ፣ የፆታዊ እኩልነት፤ ሴቶችን ለስልጣን ማብቃት፣ መሃይምነትን መቀነስ፣ የድህነትና የምግብ እጥረት ጉዳዮችን ምላሽ መስጠት እና የኢትዮጵያ ህፃናት ጥራት ያለው ትምህርት እና ጤና አግኝተው አምራችና ከአካባቢያቸው ጋር ተስማምተው እንዲኖሩ ማስቻል ማለት ነው፡፡

የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት በርካታ ባለድርሻ አካላትን ማንቀሳቀስ እና ልዩ ልዩ የልማት ዘርፎችን እና ስርዓተ ፆታን ባካተተ መልኩ የረጅም ጊዜ ስልቶችንና መር-ግብሮችን ቀርፆ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡ ይህንን ይበልጥ አስፈላጊ የሚያደርገው ደግሞ የአብዛኛዉ ድሃ ህብረተሰብ ኑሮ ከተፈጥሮ ሃብት ጋር የተያያዘ መሆን ነው፡፡ የምዕተ አመቱ የልማት ግቦች መሳካት ለኢትዮጵያ ወሳኝ እንደመሆናቸው መጠን እ.ኤ.አ. ከ2008 ጀምሮ ለአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች ቀዳሚ ስፍራ መስጠት ነበረበት፡፡ አሁንም ቢሆን ግቦቹ ይሳኩ ዘንድ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይን ትኩረት መስጠት ይገባል፡፡ በኢትዮጵያ የተደረገው የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት እንዳመለከተው ከሆነ ግቦቹን ከአገሪቱ የልማት መርሀ-ግብሮችና ፕሮግራሞች ጋር አጣጥሞ መሄድ አማራጭ የለውም፡፡

የምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች ለልማት አጠቃላይ ማዕቀፍ ይሁኑ እንጂ በድርጊት መርሃግብር የተዘረዘሩ አይደሉም፡፡ ሆኖም የድህነት ቅነሳ እስትራቴጂ ሰነዶች የምዕተ አመቱን የልማት ግቦች ወደ ተጨባጭ ዓላማዎች በመመንዘር ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ቁልፍ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እንደዚህ ዓይነቱ የመካከለኛ ጊዜ የብሔራዊ አቀጣጫ አመላካች መርሀ-ግብር አነስተኛ ገቢ/በጀት ያላቸው አገሮች ዕድገታቸውን የሚያፋጥኑ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞችን እንዲያወጡ፣ የአገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉና ድህነትን እንዲቀንሱ ያግዟቸዋል፡፡ በመሆኑም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ተገቢውን ትኩረት ያገኙ ዘንድ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂክ ሰነዶቹ ከአየር ንብረት ለውጥ አንፃር ተቀሳኝተው ሊቀረፁ ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂክ ሰነዶች የሃገር ውስጥና እንደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ ዓለም ባንክ፣ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋም፤ የመንግስታት ትብብር እና የውጭ ባለድርሻ አካላትን ባካተተ መልኩ በአባል አገራት አሳታፊ ሂደት የተዘጋጁ ዝርዝር ሰነዶች በመሆናቸው የማስፈጸሚያ ሃብት ለማሰባሰብ ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ የድህነት ቅነሳ ስልታዊ ሰነድ በአምስት ዋና ዋና መርሆዎች ላይ በመመስረት የተዘጋጀ ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ ሀገር- መር መሆኑ (country driven)፣ ሲቭል ማህበራት፣ የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን እና የግሉን ክፍለ-ኢኮኖሚ ባካተተና ባሳተፈ ሁኔታ መዘጋጀት እንዳለበት በዋናነት የሚጠቀሱ ጉዳዮች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያም ድህነትን ለመቀነስ ብሎም ለማስወገድ የተለያዩ ፕሮግራሞች የተቀረፁና ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ፕላንና (PRSP I)፣ እ.ኤ.አ. ከ2002 እስከ 2005 ተግባራዊ የተደረገው ዘላቂ ልማትን የማምጣት የድህነት ቅነሳ ፕሮግራም ((SDPRP)፣ ከ 2005/6-2009/10 ላሉት አምስት ዓመታት የተዘጋጀውና ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የፈጣንና ዘላቂ ልማት የድህነት ማስወገድ መርሀ-ግብር ይገኙበታል፡፡ የፈጣንና ዘላቂ ልማት የድህነት ማስወገድ መርሀ-ግብር የአገሪቱ መሪ የልማት እቅድ ሲሆን በሁለት ዙር የሲቪል ማህበረሰብ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅት ተወካዮችና በልማት አጋሮች ምክክር የመዳበር እድልን አግኝቷል፡፡

በፈጣንና የዘላቂ ልማት ድህነትን የማስወገድ መርሀ-ግብር (PASDEP) በአገር አቀፍ ደረጃ የሚደረገውን የልማት፣ የድህነት ቅነሳና የአየር ንብረት ለውጥ አጀንዳዎችን በማስተሳሰር ለማቀድና ለመተግበር ቁልፍ ሚና አለው፡፡ ይሁንና እስካሁን የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂክ ሰነዱ ውስጥ የማካተቱ ሂደት በቂ አለመሆኑን በርካታ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ ይህም በቀጣይነት የአየር ንብረት ለውጥን በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ውስጥ መካተት እንዳለበት ያመላክታል፡፡ የድህነት ቅነሳና አገር አቀፍ የልማት ስትራቴጂዎች የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይን ቸል የሚሉ ከሆነ ድህነትን ለመቀነሰ የሚደረጉ ጥረቶች ውጤት አልባ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የፈጣንና የዘላቂ የልማት እና የድህነት ቅነሳ መር-ግብር ሰነድ በአየር ንብረት ለውጥ ሂደቶችና ይዘቶች፤ በሌላ በኩል ደግሞ በድህነት ቅነሳ ወይም አገር አቀፍ የልማት መርሃግብር መካከል ያለውን ተያያዥነት የማመላከት ውሱንነት ይታይበታል፡፡ በመሆኑም ይህ አጭር ጥናታዊ ዳሰሳ በቀጣይነት በሚዘጋጁት የድህነት ቅነሳ እስትራቴጂ ሰነዶች ውስጥ መካተት ያለባቸውን ዘርፎች ለይቶ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ስለእያንዳንዱ ዘርፍም ያሉትን ዝርዝር ጉዳዮችና

የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች አስፈላጊ ናቸው ብለው ያመኑባቸውን ጉዳዮችም አመልክቷል፡፡ በአገር አቀፍ የልማት መርሃግብሮች እና ሂደቶች ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥን ማካተት ለውጡ በድህነት ቅነሳው ብሎም በአገሪቱ ልማት ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተፅእኖ ለመቀነስ ከወዲሁ አቅዶ ለመንቀሳቀስ ያግዛል፡፡ ይህ የዴስክ ጥናት የአየር ንብረት ለውጥ በሀገሪቱ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂ ሰነዶች ላይ መካተትና አለመካተቱን ገምግሞአል፡፡ የተገመገሙት ሰነዶችም ፈጣንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ድህነትን የማስወገድ ዕቅድ እና በተለያዩ ጊዜ የወጡ አመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርቶች ናቸው፡፡ ከግምገማው ውጤት ለመገንዘብ እንደተቻለው የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ ከወዲሁ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ከዳሰሳው የጥናት ውጤት ለመገንዘብ እንደተቻለው በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይን በአገር አቀፍ የልማት መርሃግብሮች ውስጥ አካቶ የመንቀሳቀስ ጉዳይ ገና በጅምር ላይ ያለ መሆኑን ነው፡፡ በተለይም የአየር ንብረት ለውጥ የድህነት ቅነሳ የልማት ግቦችን ከማሳካት አንፃር ያለው ተፅዕኖ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ባለው የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂክ ሰነድና በዓመታዊ ሪፖርቶች ውስጥ በቂ ትኩረት አላገኙም፡፡ የመሬት አጠቃቀም፤ የመሬት ሽፋን ለውጥ እና የመሬት ይዞታ ጉዳዮች ከተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር ጋር ያላቸው ግንኙነት፤ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ስላላቸው ፋይዳ ሰነዱ ውስጥ የተሰጠው ትኩረት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ የውሃና የብዙሃ ህይወት ጉዳዮች በሰነዱ ውስጥ በተወሰነ ደረጃ ተካክተዋል:: ነገር ግን የተነሱት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ መልኩ ሳይሆን በተናጠል ኘሮግራምነት ነው፡፡ የድህነት እና የተፈጥሮ ሃብት መጎሳቆል ቁርኝት ተገቢውን ስፍራ የተሰጠው ሲሆን የድህነትና የአየር ንብረት ለውጥ ተያያዥነት ግን ትኩረት አልተሰጠውም፡፡ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ድህነትን ለማስገወድ በተቀረፀው ሰነድ (PASDEP I) ውስጥ ፅዱ የልማት አሰራርን (Clean Development Mechanisms) የማጎልበት እና የማስፋፋት አስፈላጊነት ተጠቅሷል፡፡ ነገር ግን ይህ ስራ በአመታዊ አፈጻጸም ሪፖርቶቹ እንደታየው በቂ ስፍራ በተከታታይነት አልተሰጠውም፡፡ በአገሪቱ ያለውን የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር ለማጠናከር ስለሚረዱ አበረታች ዘዴዎች ጉዳይም የተጠቀሰ ነገር የለም፡፡ ከተፈጥሮ ሃብት አስተዳደር ጋር በተገናኘም በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ካፒታል ላይ የሚደረጉ አስፈላጊ ኢንቨስትመንቶችን የሚመለከቱ ጉዳዮችም ታሳቢ አልተደረጉም፡፡

የድህነት ቅነሣ እስትራቴጂ ሰነዱ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ለሚደረግ ያልተማከለ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ከተሰጠው አፅንኦት አንጻር ማህበረሰቡን የሚያሳትፉ በቂ ዘዴዎች እንዳሉ ያመለክታል፡፡

ሆኖም በተዳሰሱት ሰነዶች ውስጥ የተፈጥሮ ሃብት አስተዳደርን በተመለከተ የማህበረሰቡ ተሳትፎ እስከ ምን እንደሆነ የተገለፀ ነገር የለም። በሰነዱ ውስጥ በልዩ ልዩ ደረጃዎች ባሉ በእርሻ፣ በገጠር ልማት፣ በጤና፣ በትራንስፖርት እና በትምህርት ዘርፎች የፆታ ልዩነትን ለማጥበብ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ያመለከተ ቢሆንም የአየር ንብረት ለውጥ ከፆታ አንፃር ያለው ሁኔታ ግን ትኩረት አላገኘም። ልዩ ልዩ ህጎችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን በተመለከተ የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በሰነዱ የተመለከተ ቢሆንም የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ ግን በአመታዊ የአፈጻጸም ሪፖርቶቹ አልተጠቀሰም።

በሌላ በኩል የአገሪቱ አጠቃላይ ልማት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የመላመድና የመቋቋም ዘዴ አማራጭ መሆኑ ቀርቶ ወሳኝ ጉዳይ ሆኗል። ኑሮአቸው በእርሻ ላይ የተመሰረቱ ህዝቦች ለዘመናት ራሳቸውን ከአየር ንብረት መለዋወጥ ጋር አብረው የሚያስኬዱባቸው የተለያዩ ብልሃቶችንና ዕውቀቶችን ያካበቱ ከመሆናቸው አንፃር ራስን ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ማላመድ አዲስ ክስተት አይደለም። ነገር ግን የወቅቱ ፈጣን አየር ንብረት ለውጥ ግን ህዝቦች ያልተዘጋጁበትና መቋቋም የማይችሉበትን ፈተና ይዞ ተጋርጦባቸዋል። ስለዚህ ከለውጡ ጋር መሄድ የሚያስችሉ አፋጣኝ ዘዴዎችንና ብልሀቶችን መቀየስ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም። ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ለመላመድ ስልቶችንና ዘዴዎች መቀየስና ከልማት ጋር ማቀናጀት ጠንካራ ተደጋጋፊነት አላቸው። በአግባቡ የታቀደ የልማት እንቅስቃሴ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር አብሮ ለመሄድ አዎንታዊ ሚናን ይጫወታል። የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ስኬታማነት በአገሪቱ ልዩ ልዩ ደረጃዎች በሚገኙ ተቋሞች እና ማህበረሰቦች የመቋቋም ብቃት ላይ ይወሰናል። የዳሰሳ ጥናቱም ግብርናን ጨምሮ ለልዩ ልዩ ዘርፎች የሚበጁ በርካታ የመቋቋሚያ እርምጃዎችን/ ዘዴዎችን ጠቁሟል።

በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ልዩ ልዩ ገፅታዎችን የሚያመለክቱ በርካታ ኘሮግራሞችና ኘሮጀክቶች አሉ። በተለይም የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋምን (Adaptation) በተመለከተ የተዘጋጀው የአየር ንብረት ለውጥ ብሄራዊ የመቋቋምያ አፈፃፀም መርሃ ግብር (National Adaptation Plan of Action/NAPA) አንዱ ነው። ይሁን እንጂ ይህ መርሃ ግብር **(NAPA)** በአገሪቱ የብሔራዊ የልማት መርሃ ግብሮች እና ኘሮግራሞች ውስጥ በበቂ ሁኔታ አለመካተቱን ለመገንዘብ ተችሏል። ስለዚህ ይህ አጭር የዳሰሳ ጥናት በቀጣይ ጊዜያት እንዲህ ያሉ ጠቃሚና አስፈላጊ ኘሮግራሞችን በአገሪቱ የልማትና የድህነት ቅነሳ መርሃግብሮች ውስጥ አዋህዶ ለማስኬድ ጠንካራና በቂ ጥረቶች መደረግ እንዳለባቸው ይጠቁማል። ይህንን ለማድረግ

የሚያስችሉ በርካታ መልካም አጋጣሚዎች መኖራቸውንም ያመላክታል። በብሄራዊ መቋቋምያ መርሃ-ግብር (NAPA) ዝግጅት በኢትዮጵያ ሂደቱን ከታሰበለት ግብ/ዓላማ ከማብቃት እና የህብረተሰቡን ተሳትፎ ከማረጋገጥ አንፃር ጉልህ ግድፈቶች እንደነበሩበት ያመለክታል። ስለዚህ ብሄራዊ የመቋቋሚያ መርሃ ግብርን (NAPA) እንደገና መፈተሽና በእቅዱ የተቀመጡት የመቋቋሚያ ግምታዊ ዋጋዎች (Adaptation Cost) ወቅታዊውን የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖ ያገናዘበና በብቃት ለውጡን ተቋቁሞ የመሄጃ ብልሃቶችን ባካተተ መልክ እየተሻሻለ መሄድ ይኖርበታል። ቀጣይ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋምያ ኘሮግራሞችን በወቅታዊ መረጃና እውቀት ላይ መመስረት ይቻል ዘንድ ስለ ብሄራዊ የመቋቋሚያ መርሃ ግብር (NAPA) ሰፊ ግንዛቤን በልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት ዘንድ የመፍጠር ስራም መከናወን ይኖርበታል። የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች በብሔራዊ የልማት ኘሮግራሞች ብቻ ሳይሆን በየዘርፉ በሚነደፉ ኘሮግራሞችና ፖሊሲዎች ውስጥ መካተታቸውን ለማረጋገጥ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በሚያያዝ በማንኛውም እንቅስቃሴ ውስጥ በተሰማሩ ተቋሞች፣ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች/Agencies/ መካከል በቂ ቅንጅት መፈጠር ይኖርበታል።

ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ ከተመደቡ ድጋፎች ገንዘብ የምታገኝበትና ለሚሊዮኖች የኑሮ ሁኔታ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ዘዴዎች መቀየስ ይኖርበታል። የአቅም ግንባታን በማካሄድ በቂ ድጋፍ የሚገኝበትን እና ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ ማረጋገጥ ይገባል። የመቋቋሚያ እቅዶችና የአፈፃፀም ኘሮግራሞቹ ከአጠቃላይ የአገሪቱ የልማትና ድህነት ቅነሳ መርሃግብሮች ጋር መቀናጀታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል ድጋፉን የማግኘት ስራው መሰራት ያለበት ብሔራዊ እቅዶችን በሚያወጣው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ወይም ተቋም መሆን ይኖርበታል። የዳሰሳ ጥናቱ የአየር ንብረት ለውጥ እየተሰራባቸው ባሉት የአካባቢ ጥበቃና የተፈጥሮ ሀብት ፖሊሲዎችና ኘሮግራሞች ውስጥ በደንብ መካተት አለመካተቱን ለማረጋገጥ የሚያስችል ጥናት ማካሄድ እንደሚያስፈልግ ያመለክታል። ቀጣዩ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂክ ሰነድ ከመጀመሩ በፊት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ትኩረት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ እና የልማት ስትራቴጂክ ማዕቀፍ (Strategic Framework for Adaptation and Development) መዘጋጀት ይገባዋል።

ከዳሰሳ ጥናቱ ሰነድ በተጨማሪ አጥኚዎቹ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች፣ የድህነት ቅነሳ እስትራቴጂክ ሰነድንና የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች ግንዛቤን ለመፈተሽና ለመረዳት የሚያስችል ጥናት አካሂደዋል። ከጥናቱ ውጤት ለመገንዘብ እንደተቻለው

ድርጅቶቹ በጉዳዩ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ እንዳላቸውና በአንድ ወይም በሌላ መንገድ በጉዳዮቹ ላይ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለዚህ ከአጠቃላይ የዳሰሳ ጥናቱ ውስጥ ይህኛው ክፍል ከምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች፣ ከአየር ንብረት ለውጥ እና ፈጣንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ድህነትን ለማስወገድ ኢትዮጵያ ከቀየሰቻቸው መርሃግብሮች አንፃር ተቀባይነት ያላቸውን የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች እይታና ግንዛቤዎች እንዲታዩ ለማድረግ የታለመ ነው፡፡ በተጨማሪም በጥናቱ የዋና ዋና ትንታኔዎች፣ ግምገማዎች፣ የመፍትሄ ሐሳቦች፣ አስተያየቶችና መወሰድ ስላለባቸው እርምጃዎች የተሰጡ አስተያየቶችን ጨምቆ ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥንና የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ተያያዥነት በተመለከተ የልማት ግቦቹን በአግባቡ ለማሳካት የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖ ጎጂ ሚና ሊኖረው እንደሚችል የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶቹ ያምናሉ፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ካላት ዝቅተኛ የሆነ የቴክኒክና የገንዘብ አቅም አንፃር የአየር ንብረት ለውጥ ተጽዕኖን ለመቋቋም ሀገሪቷ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ እንደሆነች አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል፡፡ የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶቹ የአየር ንብረት ለውጥ ሁኔታን በሁሉም የሀገሪቷ የልማት ዘርፎች ውስጥ በማስረጽ አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድና የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በሂደቱ ውስጥ ማሳተፍ የአየር ንብረት ለውጡን ለመቋቋም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው አመላክተዋል፡፡

በተጨማሪም የዳሰሳ ጥናቱ በመረጃ የተደገፈ የፖሊሲ ሃሳብ ለማቅረብ የሚያስችል ትክክለኛ መረጃ መኖር አለመኖርን በተመለከተ ለጥልቅ ጥናት እና ምርምር ብሎም ለተሻለ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች ቅንጅት የሚያመች ተቋማዊ አሰራር መዘርጋት አለመዘርጋቱን በተመለከተ ልዩ ልዩ የፖሊሲ መፍትሄ ሃሣቦችን ይሰነዝራል፡፡ በዚህ ረገድ የብሔራዊ  እቅድ አውጭ ሚኒስቴር መስሪያ ቤትን ተቋማዊ አቅም ማጎልበት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን ጠቁሟል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዩች በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ውስጥ ተገቢውን ስፍራ ያገኙ ዘንድ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት የማሳተፍ እንቅስቃሴው ሊጠናከር ይገባዋል፡፡ በሃገሪቱ ጥልቀትና ስፋት ያለው የአቅም ግንባታ ስራም ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ከተጋረጠባት ከፍተኛ የአየር ንብረት ለውጥ ተግዳሮት አንፃር ክፍለ አህጉራዊና ቀጠናዊ ትብብርና የፖሊሲና መርሀ-ግብሮች መቀናጀትም ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

# የፖሊሲ ማሻሻያ ሐሳቦች

በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖ አደገኛና ወደ ምዕተ አመቱ የልማት ግቦች የሚደረገውን ግስጋሴ የሚገታ ብሎም ሃገሪቱ ድህነትን ለመቀነስ የምታደርገውን ጥረቶች የሚያደናቅፍ ነው፡፡ ከድህነት ቅነሳ እና ከአየር ንብረት ለውጥ ችግሮች ጋር የሚደረገውን ትግል በአሸናፊነት ለመወጣት በቀጣዩ የዘላቂ ልማትና የድህት ቅነሳ እስትራቴጂ ዕቅድ ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖን የመከላከል ጉዳይ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ በዳሰሳ ጥናቱ መሰረት የሚከተሉት የፖሊሲ ማሻሻያ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡

## <u>ጥናትና ምርምር</u>

የአየር ንብረት ለውጥ ኢትዮጵያን በከፍተኛ ሁኔታ ያጠቃታል፡፡ ያም ሆኖ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖዎችን በተመለከተ በቂ መረጃዎች የሉም፡፡ በመሆኑም ለድህነት ቅነሳ የሚነደፉ ፖሊሲዎች በተጨባጭ መረጃ የተደገፉ እንዲሆኑ ለማስቻል የአየር ንብርት ለውጥ ተፅእኖና የሚያስከትላቸውን ወጪዎች በተገቢው ሁኔታ መረዳት ያስፈልጋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖን ተቋቁሞ መቀጠል ለነገ የሚባል ጉዳይ አይደለም፡፡ ፈጣንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ድህነትን የማስወገድ እቅድ (PASDEP) ውስጥ የተካተቱ ልዩ ልዩ ዘርፎችን ጨምሮ በየደረጃው (በአገር፤ በክልል፤ በወረዳና በፕሮጀክት ደረጃ) ያሉ ዘርፎች የአየር ንብረት ለውጥን የመቋቋም ፍላጎትና አቅም እንዲሁም መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች እና የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ መጠን (በጀት) የሚያሳዩ ጥናትና ምርምሮች መካሄድ አለባቸው፡፡ በአገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያደርሰውን አደጋ ለመቋቋም የሚያግዝ ዕምቅ አቅምና ሃብት መጠናት ይኖርበታል፡፡ በአገሪቱ ለሰዎች መፈናቀል ዋነኛ መንስኤ ከሆኑ የተፈጥሮ አደጋዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን የማሰባሰብና የማደራጀት ስራ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ በየዘርፉ በሚወጡ ልዩ ልዩ ፖሊሲዎች እና ፕሮግራሞች ውስጥ በሚገባ መካተታቸውን ለማረጋገጥ እና ይሄንኑ በአጠቃላይ ከአገሪቱ የልማት መርሃግብሮች ጋር ምን ያህል እየተቀናጁ እንደሆነ የሚያመለክት ጥናትና ምርምሮች መካሄድ አለባቸው፡፡ የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮችን በአገሪቱ የልማት ዕቅድ ውስጥ በሚገባ ለማካተት አመቺና አደናቃፊ ሁኔታዎችን ለይተው የሚያሳዩ የምርምር ውጤቶችም ያስፈልጋሉ፡፡ ይህንን በማድረግ ለአየር ንብረት ለውጥ የማያስፈልገው አግባብነት ያለው ምላሽ እና በልማት መርሃግብሮች

መካከል ያለውን ትስስር ለመረዳት እንዲሁም የጉዳዮቹን መካተት (ትኩረት ማግኘት) ሂደት ስኬታማነት ማረጋገጥ ያስችላል፡፡ ወደምዕተ አመቱ የልማት ግቦች የሚደረገው እርምጃ ከአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ አንፃር በመገምገም ያሉበትን ደረጃና አዝማሚያ የሚያሳዩ እና ለግቦቹ መሳካት መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች የሚያመላክቱ የጥናትና ምርምር ውጤቶችም ያስፈልጋሉ፡፡

## የመረጃ ፍሰትና ግንዛቤን ማሳደግ

ለተሳካ ከአየር ንብረት ለውጥ የመቋቋም አቅም መረጃና ግንዛቤ ወሳኝ ናቸው፡፡ ስለዚህ በጥናትና ምርምር የተደገፈ እና የተጠናከረ ጥረት በማድረግ ለፖሊሲ አውጪዎች እና ህብረተሰቡን ጨምሮ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ ተገቢውን መረጃ በማድረስ ረገድ በቂ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች እና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች ስላላቸው ሚና የሚያሳዩ መረጃዎችን በአመት ሁለት ጊዜ ለልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት ማድረስ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የአየር ንብረረት ለውጥን ለመቋቋም ለሚደረጉ ጥረቶች በቂ ትኩረት እንዲሰጡና በበለጠ እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋቸዋል፡፡

ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ለማሰራጨት የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (Information and Communication Technologies) መሳሪያዎችን መጠቀም እጅግ በጣም አስፈላጊና ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ የኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች፣ ከድህነት ቅነሳና ዘላቂ ልማት መርሀ-ግብር እስትራቴጂክ ሰነድ እና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ አስፈላጊ መረጃዎችን በስፋትና በብቃት ለማዳረስ የሚያገለግሉ በመሆኑ አግባብነት ባላቸው መረጃ አመንጪ በሆኑ ዘርፎች ውስጥ ግልጋሎት ላይ መዋል የሚገባው ሲሆን ይህንንም የሚያስተባብር ተቋም ሊደራጅና ሊጠናከር ይገባዋል፡፡

## ተቋም

የአገሪቱን የፖሊሲ አወጣጥ ስርዓት ለመደገፍና ለማጠናከር የሚያስችል ብሄራዊ የአየር ንብረት እና የአካባቢ ጥናትና ምርምር ኤጀንሲ በተቻለ ፍጥነት መመስረት ይኖርበታል፡፡ ይህንን አሁን ያሉትን ተቋማት ስልጣንና ሚና ማጠናከርና ማስፋት ወይም አዲስ ተቋም መመስረት ሊሆን ይችላል፡፡ የሚቋቋመው ተቋም በቴክኒክና በገንዘብ አቅም የተጠናከረ፤ በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች የተዋቀረ መሆን ይኖርበታል፡፡ ተቋሙ የአየር ንብረት ለውጥ ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖዎችን

የመገምገም እና ተፅዕኖዎችን የመቋቋሚያ አማራጮችን የሚያጠና ፈጣንና ዘላቂ ልማትን በማረጋገጥ ድህነትን ለማስወገድ በየዘርፉ የሚደረጉ ጥረቶችን አፈፃፀም ለማሻሻል በየደረጃው ላሉ አካላት አቅጣጫ ጠቋሚ የመፍትሄ ሃሳቦችን የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡

ይህ ተቋም የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖዎችን እና ተፅእኖዎችን የመቋቋም ብቃት ደረጃ በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ከመከታተል በተጨማሪም የአየር ንብረት ለውጥ የመቋቋምና ልማትን ያስተሳሰረ እስትራቴጂክ ማዕቀፍ(Strategic Framework for Adaptation and Development) መቅረፅ ይኖርበታል፡፡ ይህ ማዕቀፍ ለአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች በአገር አቀፍ የልማት መርሃግብሮች ውስጥ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ በቂ አቅጣጫን የመጠቆም ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ማዕቀፉ በአገሪቱ ውስጥ ለሚከናወኑ ማናቸውም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ለተያያዙ ድርጊቶች አቅጣጫ የመስጠት ሚና ይኖረዋል፡፡ አሁን ያሉትን ተቋማት እንደገና ማዋቀር የአየር ንብረት ለውጥን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት(ለመረጃ አመንጪዎች፣ ለተንታኞች እና ለፖሊሲ አውጪዎች) በቀላሉ ለማድረስ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ይህ በኢትዮጵያ ለድህነት ቅነሳና ለምዕተ አመቱ የልማት ግቦች መሳካት ተግዳሮቶችን ለማሸነፍ ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥን ለሚመለከቱ ጉዳዮች ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ሲባል መደበኛ ተቋማትን የመመስረትና አዳዲስ አቅጣጫዎች የመስጠትን ያህል በታችኛው ማህብረሰብ ደረጃ ያሉትን ኢ-መደበኛ ተቋማትን ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ በሚሰጡበት መልክ እንደገና መቃኘት ያስፈልጋል፡፡

የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርም በአገር አቀፍ የልማት መርሃግብር ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች አተገባበር እና ቁጥጥር ትኩረት እንዲሰጥ ለማድረግ ተቋማዊ አቋሙ ሊጠናከር ይገባል፡፡ በተመሳሳይ መልክ በክልል፣ በወረዳ እና በቀበሌ ደረጃ ያሉ ተቋማት አቅማቸው መጠናከር ይኖርበታል፡፡

## ማቀናጀት እና ማስረፅ

የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በሃገራዊ የልማት መርሃግብሮች፣ በዘርፍ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ውስጥ ማስረፅና አቀናጅቶ ማስኬድ የአየር ንብረት ለውጡ

ለሚያስከትላቸው ተፅእኖዎች አግባብ የሆነ ምላሽ ለመስጠት አስፈላጊ ነው፡፡ የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ የሚወሰዱ እርምጃዎችን ማስረፁ የሚጠቀመው በአገር አቀፍ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በአካባቢ፣ በክልል እና በፕሮጀክት ደርጃ ጭምር ነው፡፡ የአየር ንብረት ጉዳይን ለማስረፅ የሚያግዙ የመረጃ፣ የተቋም፣ የቴክኒክ እና የገንዘብ አቅም ክፍተትን የመሳሰሉ መሰናክሎች በበቂ ሁኔታ ምላሽ ማግኘት አለባቸው፡፡

በአገሪቱ ብሄራዊ የመቋቋም አፈፃፀም መርሃ ግብር (National Adaptation Programme of Actions) እና የድህነት ቅነሳ እስትራቴጂዎች (Poverty Reduction Strategies) ውስጥ የተሻሉ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ ፕሮግራሞችን ለማካተት በቂ ሁኔታና መልካም አጋጣሚዎች በመኖራቸው አስፈላጊነቱ አሌ አይባልም፡፡ አገሪቱ በቀጣይ ጊዜያት በምታወጣቸው ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥን የማካተት ጉዳይ በቂ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

በአካባቢና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ረገድ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይን በቀዳሚነት መካተት ሃገሪቱ የምዕተ አመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት በምታደርጋቸው የልማት ጥረቶች የተጋረጡብንን መሰናክሎች በአሸናፊነት ለመወጣት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ የምዕተ አመቱን የልማት ግቦች በክልል፣ በዞን እና በወረዳ የልማት ዕቅዶችና መርሀ-ግብሮች ውስጥ ማካተትና ተፈላጊውን በጀት መመደብ የግቦችን ወደ ስኬት የማድረስ ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡

## <u>የገንዘብ ድጋፍ</u>

ለአየር ንብረት ለውጥን አስመልክቶ ጥናትና ምርምር ለማድረግ የገንዘብ ድጋፍ በበቂ ሁኔታ መጨመርና የመንግስት፣ የግልና የማህበረሰብን ድጋፍ በሚያገኝበት መልክ መስፋፋት ይኖርበታል፡፡ የምዕተ አመቱን የልማት ግቦች የማሳካት አቅም ለማሳደግ፣ ለመቆጣጠርና ለመጠቀም የሚረዱ አነስተኛ ጥናት እና ምርምሮች ለማጎልበት የተጠናከረ የገንዘብ ድጋፍ መደረግ አለበት፡፡ አገሪቱ የድህነት ቅነሳ አላማዎቿንና የምዕተ አመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የተያያዘቸው ግስጋሴ እንዳይስተጓጎል አስተማማኝ ሁኔታ ለመፍጠር በየደረጃው ከፍተኛ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ እና መቀነሻ ድጋፍ የማሰባሰብ እንቅስቃሴ ሊደረግ ይገባል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም ተብለው የተቋቋሙትን የገንዘብ ድጋፎች በተገቢው መንገድ የሚገኙባቸውን ሁኔታዎችና የተገኙትንም ድጋፎች በተገቢው መልክ ስራ ላይ

ለማዋል የሚያስችል በቂ ተቋማዊ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በአየር ንብረት ለውጥ ድርድር ሂደት ውስጥ በንቃት ከመሳተፍ አንስቶ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋምና ለመቀነስ የሚያስፈልገውን ገንዘብ አሰባሳቢ ተቋም ሆኖ መስራት ይኖርበታል፡፡ ይህም አሰራር የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ ፕሮግራሞች በአገሪቱ የልማት ማእቀፍ ውስጥ ሰርጸውና ተቀናጅተው እንዲቀረፁ ይረዳል፡፡

## ትብብርና ቅንጅት

የአገሪቱ የልማት ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት ይቻል ዘንድ የሚመለከታቸዉ አካላት ሁሉ መተባበር ይገባቸዋል፡፡ መንግስት እያዘጋጀ ባለዉ የድህነት ቅነሳ እና ዘላቂ ልማት መርሀ-ግብር ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይን ተገቢውን ቦታ ለመስጠት እንዲሁም ውጤታማ አተገባበር እንዲኖራቸው ለማድረግ በሚመለከታቸው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ የክልል መንግስታት፣ የጥናትና ምርምር ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪክ ማህበረሰቡ እና ለጋሽ ተቋማት መካከል የላቀና የተጠናከረ አብሮ ተባብሮ የመስራት ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ የድህነት ቅነሳ እና ዘላቂ ልማት መርሀ-ግብሩ ሰነድ ዝግጅት፣ ትግበራና ክትትል ላይ በሚመለከታቸው ልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ሊኖር የሚገባውን ትብብር ለማጠናከር የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ግንባር ቀደም ሚና መጫወት ይኖርበታል፡፡

አገሪቱ ልዩ ልዩ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎችን ለመቋቋም የምትወስዳቸውን እርምጃዎች ሂደቶችንና ፕሮግራሞችን በድህነት ቅነሳ ስትራቴጂክ ሰነዶቿ እና በልማት ስትራቴጂዎቿ ለማካተት የምታደርጋቸውን ጥረቶች ለመደገፍ መንግስታትና የለጋሽ ማህበረሰቦች ትብብር እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ የልማት አጋሮች ለአገሪቱ የሚያደርጉትን የልማት ድጋፍ ከድህነት ቅነሳ ስትራቴጂክ ሰነዱ ጋር በመቃኘት እና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖዎችን ከግንዛቤ በማስገባት ትብብራቸውን ከፍ ማደረግ አለባቸዉ፡፡

በልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት መካከል የሚኖረውን ትብብርና ቅንጅት ለማጠናከር የሚያስችል እና የአየር ንብረት ለውጥን የሚመለከቱ ጉዳዮችን በድህነት ቅነሳና በዘላቂ ልማት መርሀ-ግብር ውስጥ ተገቢ ስፍራ እንዲኖራቸው የሚያግዝ መድረክ በገንዘብና እና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ስር መቋቋም ይኖርበታል፡፡

## ተሳትፎ

ለድህነት ቅነሳ እና ለዘላቂ ልማት መርሀ-ግብሩ ስኬታማነት ልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት በዉሳኔ አሰጣጥ ሄደት ውስጥ የአየር ንብረት ለዉጥና የልማት ጉዳዮች ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ በየደረጃዉ ማሳደግ አስፈላጊ ነዉ፡፡ በተለይ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋም ጉዳዮችን በተመለከተ በሚደረጉ የዉሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ በዋናነት ተጠቂ የሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎችን በቀዳሚነት ሊያሳትፍ የሚያስችል ዘዴ መቀየስ ይኖርበታል፡፡

## አቅም ግንባታ

ጥራት ያለዉ የአየር ንብረት መረጃን ለማግኘት እና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖን በሚገባ ለመከታተል በሚያስችል መልክ አቅምን የመገንባት አቅጣጫ መከተል ይገባል፡፡ ይህን ማድረግ በየጊዜዉ የሚለዋወጠዉን የአየር ንብረት አዝማሚያ ለመከታተልና ለመቆጣጠር እንዲሁም በሂደት ሊከሰቱ የሚችሉ የአየር ንብረት ለዉጥ ተፅእኖዎችና በየደረጃዉ ሊተኮርባቸዉ የሚገቡ የመቋቋሚያ ዘዴዎችን አስቀድሞ ለመዳሰስ ያግዛል፡፡ ይህም የምዕተ አመቱን የልማት ግቦች ከማሳካት አንጻርም አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡

የአየር ንብረት ለዉጥ ጉዳዮችን በሚገባ በየደረጃው በልማት ዕቅድና ፖሊሲ ውስጥ ለማካተትና ቅድሚያ ለመስጠት እንዲሁም በልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት መካከል ሊኖር የሚገባዉን ትብብር ለማጠናከር በልዩ ልዩ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፣ ተቋማትና የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች የአቅም ግንባታ ፍላጎት መዳሰስና በየደረጃዉ ያለዉን የአቅም ግንባታ እንቅስቃሴ የአጠቃላይ የአገሪቱ መርሃግብሮች ማዕቀፍ አካል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ግንዛቤን በመፍጠርና መረጃን በማሰራጨት ከፖሊሲ አዉጪዎች እስከ ታችኛዉ የማህበረሰብ ክፍሎች ባሉ ባለድርሻ አካላት ዘንድ የአቅም ግንባታ ስራ በስፋት መከናወን ይገባዋል፡፡ የአቅም ግንባታ ስራዎች ስርዓት ባለዉ መንገድ መከናወናቸዉን ለማረጋገጥ አለምአቀፍ የአቅም ግንባታ መርሀ-ግብሮች ከአገሪቱ የልማት ማዕቀፎች ጋር እንዲጣጣሙ እና እንዲቀናጁ ማደረግ ያስፈልጋል፡፡

በልዩ ልዩ ባለድርሻ አካላት በተለይም በማህበረሰቡ ዉስጥ ለተፈጥሮ አደጋዎች ተገቢ ምላሽን መስጠት የሚያስችል የቅድመ ማስጠንቀቂያ አቅም ግንባታ መርሀ-ግብሮች በስፋት መዘርጋት ይገባዋል፡፡ በታችኛዉ የአስተዳደር እርከን ላሉ ባለሙያዎችም ስልጠናን ጨምሮ ሰፊ የአቅም

ግንባታ ስራ መከናወን ይኖርበታል፡፡ የአየር ንብረት ለውጥ መቋቋሚያ መርሀ-ግብሮች አፈፃፀምን ለማጎልበት እና ለአየር ንብረት ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለማስፋፋት የሚያግዙ የአቅም ግንባታዎች ሊከናወኑ ይገባል፡፡

በተጨማሪም የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የአየር ንብረት ለዉጥ ተፅዕኖዎችን ባካተተ ሁኔታ የድህነት ቅነሳ ስትራቴጂክ ሰነዶችን ለማዘጋጀት እንዲችል ተቋማዊ የአቅም ግንባታ ሊደረግለት ይገባል፡፡

## ክፍለ አህጉራዊና ቀጠናዊ ትብብሮች

የአየር ንብረት ለዉጥና የተፈጥሮ አደጋዎች የሚጋርጧቸዉ ፈታኝ ተግዳሮቶች የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን፣ መሰረተ ልማቶችን (የሃይል፣ ትራንስፖርትና መገናኛ)፣ ጥናትና ምርምሮችን እንዲሁም የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች አጠቃቀምን በተመለከተ ለሚነሱ ጉዳዮች ክፍለ አህጉራዊና ቀጠናዊ ትብብሮችን መፍጠርና ማቀናጀት የግድ ይላል፡፡

አገራዊዉ የልማት ማዕቀፍ፣ ያሉትን ትብብሮችና የአጋርነት ስነምምነቶች የሚጠናከሩበትን፣ አዳዲስ ክፍለ አህጉራዊና ቀጠናዊ ትብብሮች የሚጎለብቱበትን ግልፅ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ በድህነት ቅነሳ ፕሮግራሞች ብሎም ለአየር ንብረት ለዉጥ ተፅዕኖዎች ተገቢውን ምላሽ መሰጠት አለበት፡፡ የአገሪቱን የልማት አጀንዳዎች ማስቀጠል እና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያያዥነት ላላቸዉ ጉዳዮች ተገቢ ምላሽ የሚሰጡ ጥረቶችን ለማስተባበር ይቻል ዘንድ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ህብረት (African Union)፣ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ቡድን (Least Developed Countries group)፣ በአፍሪካ ሚኒስትሮች የአካባቢ ኮንፈረንስ (African Ministerial Conference on the Environment) እና በሌሎች የመንግስታት እርስ በርስ ትብብር ተቋማት ውስጥ የሚኖራትን ሚና በተመለከተ ግልፅ አቅጣጫዎችን ማስቀመጥ ይገባል፡፡